# ስለመሃይምናን ትምህርት የተደረገ ጥናት

## መ ግ ቢ ያ ።

ይህ ድርሰት የተዘጋጀው ለ «ብሔራዊ መሃይምናን ትምህርት ጉባኤ» ለውይይት መነሻ እንዲሆን ተብሎ ነው።ጥናቱ የተደረገው በአንድ ወር ተኩል ጊዜ ውስጥ ስለሆነ ፤ የመሃይምናንን ትምህርት ሁናቴ ፤ ጨርሶ አጠና ለማለት አይቻልም ። ከአዲስ አበባ ፴፯ ያህል ድርጅቶችና ትምህርት ቤቶች ጋር በመ ጠይቅ አማካይነት ግንኙነት አድርጓል ።

ከየጠቅላይ ግዛቱ የተውጣጡ ፩፻፺፯ የዩኒቨርሲቲ አገልግሎት አስተማሪ ዎች የ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ሪፖርት ተመልክተናል ። ሁሉም ስለመሃይምናን ትምህ ርት ያወሳሉ ። ግን ከእነዚህ ፩፻፵፰ቱ የሚያወሱት ፤ በ፳፱ ቦታዎች የመሃይም ናን ትምህርት የ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. እንዴት እንደሚካሔድ የገጠመውን ችግርና መፍትሔውን በመጥቀስ ነው ።

በተጨማሪ ስለመሃይምናን ከየመሥሪያ ቤቶች የተጻፉትን ጽሑፎች ሪፖ ርት ፤ ጥናቱ ተመልክቶአል ። በየትምህርት ቤቱ የመሃይምናንን ትምህርት በተ ቻለ መጠን ለመጐብኘትና ለመረዳት ተሞክሮአል ።

ከነዚህም ምንጮች በተገኘው መሠረት ፤ ጥናቱ የመሃይምናንን ትምህርት ሁናቴ ፤ ችግርና ይሆናል የተባለውን መፍትሔ ያቀርባል ።

አንባቢውን በጥቃቅን ድርጊቶችና በዝርዝር ነገርና ሐሳብ ከማሰልቸት ይልቅ ፤ በአጠቃላይ መልክ ፤ ጠቅላላውን አቅዋምና የመሃይምናን ትምህርት ያጋጠመውን ለማመልከት ሞክሮአል ።

ይህ ጥናት የተከናወነው በብሔራዊ ፊደል ሠራዊትና በቀ- ኃ- ሥ- ዩ- «ኤዱኬሽን ፋኩልቲ» ትብብር ነው ። ጥናቱን በማካሔድ የለፉትን

አቶ ኑር ሑሴንን
አቶ ግርማ ሥዩምን
አቶ አዳሙ ዋለልኝን
አቶ አክሊሉ ያደቴን
አቶ አበራ መኰንንን
አቶ ሙሉጌታ አራጌንና
አቶ አሸናፊ ሞገስን

በጣም አመሰግናለሁ ።

አዘጋጅ ፤
ኃይለ ገብርኤል ዳኜ

# የመሃይምናን ትምህርት ዓላማ

በየቦታው የሚገኙ የመሃይምናን ትምህርት ፕሮግራም ያላቸው ድርጅቶችና ተማሪ ቤቶች ለምን እንደሚያስተምሩ ተጠይቀው ነበር ። መልሳቸውን ብናጠቃልለው እንደሚከተለው ሆኑ ።

፩- በቀለም ትምህርት አማካይነት ድንቁርናን ለማጥፋት
፪- በበጎ አድራጎት መንፈስ ተነሣሥተው ያልተማሩትን ለመርዳት
፫- ያልተማሩት መሃይምናን ተምረው በሀገሪቱ የኤኮኖሚ እድገት እንዲሳተፉ ለማድረግ
፬- አዋጅንና ትእዛዝን ለመፈጸም ብለው
፭- የተማረ ሁሉ ያልተማረን የማስተማር ግዴታ ስላለበት
፮- ለመሥሪያ ቤቱ ጥቅም ለማትረፍ ሲሉ ።

፩- የመሃይምናን ፕሮግራም ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ከዳር እስከ ዳር የሰጡት መልስ ፤ ሁሉ እንዲማርና ድንቁርና እንዲጠፋ ሲባል የመሃይምናንን ትምህርት ፕሮግራም መጀመሩን ነው ። አለመማር እንደ ድንቁርና ይቈጠራል ፤ ስለዚህ ይህን ለማስወገድ ያልተማሩትን ለማስተማር ሲባል ፕሮግራም ተጀመረ የሚለው ሐሳብ ተደጋግሞ ይጠቀሳል ። አለመማር ሲባል በተለይ የቀለም ትምህርትን ነው ። የቀለም ትምህርት በፊደል ፤ ንባብና ጽሕፈት ትምህርት ይጀመራል ። ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን እንጠቅሳለን ።

«-----የሰው ዘር በተፈጥሮ ከሚያውቃቸው አንዳንድ ኢምንት ነገሮች በስተቀር በአእምሮ ፍልስፍና በልጽጎ ፤ በጥበብ ተራቅቆ ፤ እርቆ ማስተዋል ክፉውንና ደጉን ለመለየት መብቱን ፤ ግዴታውን ለመገንዘብ የሚያስችለው ማንበብና መጻፍን እንዲሁም መሠረታዊ ስሌትን «አራቱን መደብ ሂሳብ» በቀደምትነት አውቆ ሲገኝ ነው ። (ሸዋ ጠ/ ግዛት ጽ/ ቤት መሃይማናን ት/ ሥራ ውጤት መግለጫ ፤ ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ገጽ ፩/

፪- አንዳንዶችም ላይ የተገለጸውን ዓላማ ተደግፈው ፤ በበጎ አድራጎት ስሜት ተነሣሥተው ፤ የመሃይምናንን ትምህርት ፕሮግራም አዘጋጅተዋል ። ለመማር ዕድል ያላገኙትን ወጣቶች ወይ ጐልማሶች ለማስተማር ሲሉ ፕሮግራሙን ይጀምራሉ ። በመሠረቱ ሐሳባቸው ድኆችን ለማስተማር ነው ። እናት አባት የሌላቸውን ልጆች ወይም በሊስትሮነት ፤ በአሽከርነትና በቀን ሞያተኛነት የተሠማሩትን በትምህርት በኩል ለመርዳት የተነሣሡ ናቸው ።

፫- ተጨማሪ ሆኖ የሚጠቀሰው ዓላማ ደግሞ መሃይምናንን አስተምሮ ራሳቸውን ለማስቻል ፤ ኑሮአቸውን ለማሻሻል እንዲሁም ፍሬ አፍርተው ለሀገሪቱ የኤኮኖሚ እድገት እንዲያተርፉ ሲባል ነው ።

፬- አንዳንዶችም መሃይምናንን ለማስተማር ስለታዘዙ ትእዛዙን ለመፈጸም ሲሉ ብቻ ማስተማራቸውን ሲገልጹ ፤ ሌሎች ደግሞ በበጎ ፈቃዳቸው ለመተባበር ሲሉ የሚጥሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ ።

፭- የተማረ ሁሉ ያልተማረውን ወገኑን የማስተማር ግዴታ አለው ብለው ለማስተማር የተነሡም አሉ ። ይህ የሞራል ግዴታ ፤ የመሃይምናንን ፕሮግራም ለሚመሩት አንዳንድ ሰዎችና መሥሪያ ቤቶች ጥረት መነሻ ነው ።

፮- ተመጠኑ በርከት ያሉ የግል ድርጅቶች ፋብሪካና ትምህርት ቤቶች መሃይምናንን የሚያስተምሩት ጥቅም ፍለጋ ነው ። ፋብሪካዎች ንባብና ጽሕፈት ወይም ትንሽ ሂሳብ በማስተማር ሠራተኛው ሥራውን በተሻለ ያከናውናል በሚል ተስፋ ነው ። የግል ትምህርት ቤቶች ግን ዝናቸውና ስማቸው በአካባቢው እንዲገነን ሲሉ መሃይምናንን አልፎ አልፎ በነፃ ያስተምራሉ መሃይምናኑም ትንሽ ከተማሩ በኋላ ፤ የትምህርት ፍላጎት አድሮባቸው ከሁለተኛ ክፍል ጀምሮ እንዲከፍሉና እንዲማሩላቸው ሲሉ ፤ ከሌላ ሥራቸው ጋር ደርበው በመጠኑ ያስተምራሉ ።

## ለመሃይምናን የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች

የመሃይምናን ትምህርት ፕሮግራም ያላቸው መሥሪያ ቤቶች የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ተመሳሳይ ነው ። ፊደል ቈጠራ ፤ አማርኛ ንባብና ጽሕፈት ፤ መጀመሪያውን ደረጃ ይዟል ። ቀጥሎ ሂሳብ ፤ ከዚያም እንግሊዝኛ ያስተምራሉ ። አልፎ አልፎ የሞያ ነክ ትምህርት የሚሰጡ አሉ ። የሚበዛው ግን የሴቶች ባልትናና ሐይጅን ነው ። ሞያ ነክ ትምህርት የሚሰጡት መሥሪያ ቤቶች ብዙዎች ለዚሁ ዓላማ የተቋቋሙ ናቸው ። ዋና ዋኖቹም የትምህርት ሚኒስቴር ሙያ ነክ ትምህርት ፤ ሕዝባዊ ኑሮ እድገት ጣቢያዎች ፤ የሴቶች ማኅበሮች ፤ በተለይ የዳበረ የሙያ ነክ ትምህርት ይሰጣሉ ። በቀሩት ፕሮግራሞች ቀለም ትምህርት እጅግ ያይላል ። ከተጠየቁት መሥሪያ ቤቶች የተገኘው የትምህርት ዝርዝር እንደሚቀጥለው ነው ።

ለመሃይምናን የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች

| | |
|---|---|
| የአማርኛ ንባብና ጽሕፈት | ሙያ ነክ |
| ሂሳብ ፤ | ባልትና ፤ የሕፃናት አስተዳደግ ፤ |
| እንግሊዝኛ | ግብርና ፤ ንግድ ፤ ውትድርና |
| ሐይጅን | |
| ጂኦግራፊ | |
| ታሪክ | |

ከነዚህ ላይ ከተጠቀሱት ትምህርት ዓይነቶች መሃይምናን ተማሪዎች የቱን ይበልጥ ይወዳሉ ። የቱስ ፍላጎታቸውን ያረካል ተብሎ ተጠይቆ ነበር ።

አንዳንድ መሥሪያ ቤቶች መሃይምናን የሚወዱትንና ፍላጐታቸውን የሚያረካውን ዓይነት ትምህርት ለማወቅ አቅቶአቸዋል ። ምናልባት ይህን አላሰ

ቡበት ይሆናል ። አንዳንዶች ደግሞ የተማሪዎች ምርጫ ከቦታ ቦታ ይለያያል ብለዋል ። መሃይምናን የሚወዱትን ትምህርት እናውቃለን ያሉት ፤ መጀመሪያ አማርኛ ንባብና ጽሕፈት ሁለተኛ ሂሳብ ከዚያም ቀጥሎ እንግሊዝኛ ፤ የእጅ ሥራና ሐይጅን ነው ብለዋል ። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው ።

መሃይምናን ተማሪዎች የሚወዱት የትምህርት ዓይነት

አማርኛ ንባብና ጽሕፈት
ሂሳብ
እንግሊዝኛ
እጅ ሥራ
ሐይጅን

መሃይምናን ተማሪዎች ወደዱም አልወደዱም የሚሰጣቸው ትምህርት በቅደም ተከተል ፤ ከላይ የተጠቀሰው ብቻ ነው ። ተማሪዎቹ ምርጫ የላቸውም በብዛት የቀረበላቸው አማርኛና ሂሳብ ስለሆነ ፤ ወደዚህ ያዘነበሉ ይመስላል እንጂ ከሙያ ነክ ትምህርት ይበልጥ ፤ የቀለም ትምህርት መውደዳቸውን ለማረጋገጥ የሚቻለው ፤ ቀለምና ሙያ ትምህርት ተመጣጥኖ በብዛት ቢሰጥ ነበር ። ሆኖም ማንበብና መጻፍ ፤ እንዲሁም ሂሳብ መሠረተ ትምህርት ከመሆናቸው በላይ ፤ ለተማሪዎቹ ለዕለት ኑሮ የሚያስፈልጋቸው ይመስላል ።

## የመጻሕፍትና የትምህርት መሣሪያ ሁናቴ

በየቦታው መሃይምናንን ለማስተማር ብዙዎች የሚጠቀሙት በፊደልና ንባብ ጽሑፎች ነው ። ይህም ሊሆን የቻለው እላይ እንደተገለጸው ዋናው የትምህርት ዓላማ ፊደልና ንባብ ለማስተማር ስለሆነ ነው ። መጻሕፍትን በግዢ ሳይሆን በስጦታ የሚቀበሉት ድርጅቶች ይበዛሉ ። ዋና ሰጪ መሥሪያ ቤቶች የሚቀጥሉት ናቸው ።

ፊደል ሠራዊት
ትምህርት ሚኒስቴር
የምሥራች ድምፅ
ሕዝባዊ ኑሮ እድገት

እንደሚመስለው መሃይምናን የትምህርት መሣሪያ ለመግዛት ያላቸው ዓቅምና ፍላጎት የተወሰነ ነው ። ስለዚህ ድርጅቶቹ መጻሕፍትን አዘጋጅተውም ሆነ ከሌላ ለምነው በነፃ ለማደል ይጥራሉ ።

የራሳቸውን መጻሕፍት በማተምም ሆነ በማባዛት የሚያዘጋጁ ድርጅቶች ጥቂት ናቸው ። እነዚህም እርስ በርሳቸው ግንኙነት የላቸውም ። አንዳንዶቹም ድርጅቶች በተለይ ሙያ ነክ የሆኑ ጽሑፎች ያዘጋጃሉ ። ለምሳሌ ክብር ዘበኛ ለውትድርና ፤ ሴቶች ማኅበር ባልትና ጠቀስ ያዘጋጃሉ ። በስጦታ የሚጠቀሙ መሥሪያ ቤቶች ፤ እርሻና ጤና ጠቀስ ጽሑፎችን ከሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒ

ስቴር ፤ ከእርሻ ሚኒስቴርና ከጤና ጥበቃ ያገኛሉ ። ቀለም ጠቀሱን ግን ከፊደል ሠራዊት ፤ ከት/ሚኒስቴርና ከምሥራች ድምፅ ዘንድ በግዢ ሆነ በስጦታ የሚ ያገኙ ይመስላል ።

ከጥቁር ሠሌዳና መጻሕፍት ሌላ ፤ መረጃ ያላቸው ድርጅቶች እጅግ ጥቂት ናቸው ። አንዳንዶች በተለይ በየከተማው ያሉ ፊልም በውሰት እየወሰድን እን ጠቀማለን ይላሉ ። ሌሎች ግን እንደትጋታቸውና ችሎታቸው ፤ መረጃና መግ ለጫ የሚሆኑ ሥዕላ ሥዕል ይቀርጻሉ ። ለምሳሌ ካርቶን ቀፈው ሥዕል ያዘጋ ጃሉ ። «ካርድ ቦርድ» «ፍላሽ ካርድ» «ቻርት» ዓይነት ይጠቅማሉ ። የግርግዳ ፊደላት ያላቸውም አሉ ። «ፖስተር» ና «እስትሪፕ» እንጠቀማለን ያሉ አሉ ።

በተለይ ሥራዬ ብለው የመግለጫ መሣሪያ ለማዘጋጀት የሚጥሩ ወይም የሚያስቡ የሞያ ነክ ጉልማሶች ፕሮጄክትና የምሥራች ድምፅ ድርጅቶች ናቸው ። የቀሩት ከጥቁር ሠሌዳና ከንባብ መጻሕፍት አልወጡም ።

የማስተማሪያ መጻሕፍትንና መሣሪያን ለማዘጋጀት የሚጥሩ ድርጅቶች በመዘጋጀቱ ጥበብ በማሳተሙ አንዱ ካንዱ የሚግርና የሚተባበር አይመስ ልም ። ስለዚህ ልዩ ልዩ ያልተሞከሩ መሣሪያዎች ለተማሪው ይቀርባሉ ። ለም ሳሌ ከ፳ ዓይነት በላይ የፊደል መማሪያ ዘዴ ቀርቧል ። ግን አንዱም ተፈትኖ ተመርምሮ የተሻለ ነው ተብሎ ፤ መሃይምናንን ለማስተማር አልቀረበም ። አስ ተማሪው በተለወጠ ጊዜ ወይም ተማሪው አንዱን ተማሪ ቤት ትቶ ሌላጋ ቢሔድ መሣሪያውና ዘዴው ይለዋወጥበታል ። የትምህርቱን ጥልቀት የሚቀን ሰው ፤ በተለይ ለአስተማሪው ፍቱን የሆነ መምሪያ ባለመኖሩ ነው ። ብዙዎቹ በፈቃዳቸው የሚያስተምሩት ወይም የሚቀጠሩት የዘዴ እጥረት አላቸው።ስለ ዚህ የአስተማሪው መምሪያና የተማሪው መጽሐፍ ልዩ ዝግጅት ይጠይቃል ። ስለዚህ ፤

፩/ ለየትምህርቱ ማስተማሪያ መጻሕፍት ፤

፪/ ለየትምህርቱ የማስተማሪያ ዘዴና መግለጫዎች ፤ ምርምርና ጥናት አንድ ማዕከላዊ ድርጅት ማድረግ ይኖርበታል ። የዚህም ምርምርና ጥናት ውጤት በየቦታው ተሞክሮ በሥራ ላይ እንዲውልና በብዛት እንዲታ ተም መሆን አለበት ። ይህ የሆነ እንደሆነ ኃይል ሳይባክን ጥራት ያላ ቸው መጻሕፍትና መግለጫዎች ታትመው ከብዛት የተነሣ በርካሽ ለማ ዳረስ ይቻላል ። ጥልቀትና ጥራት ያላቸው መጻሕፍትን ፤ የመሃይምናን ሥርዓተ ትምህርትንና የመማሪያ መሣሪያን አነስተኛ ድርጅቶች ሊያ ዘጋጁ ፤ ገንዘብና ችሎታ አይፈቅድላቸውም ።

እስከ ዛሬ የታተሙት የአማርኛና ሒሳብ መማሪያ መጻሕፍት ዓይነታ ቸው ብዙ ነው ። ብዙዎቹ የተዘጋጁት መልካም ፈቃድ ባላቸው ሰዎች እንጂ በምርምር የተመሠረተ አይደለም ። ለመሃይምናን ተብለው የተጻፉት ምንባብ ብዙዎቹ ታሪክና ምሳሌ ፤ ግብረገብ ፤ ሃይማኖት ጠቀስ ናቸው ። የመሃይምናንን

ሕይወት ፤ ችግርና ፍላጎት የሚያረኩ ምንባብ ለየቦታውና ሁናቴው ማዘጋጀት እጅግ ያስፈልጋል ። ይህንንም ለማድረግ የሚቻለው ማዕከላዊና ብሔራዊ ድር ጅት ነው ። ግላዊ ድርጅቶች የግል ጥቅምና እምነታቸውን በመሃይምናን ትም ሀርት አማካይነት ስለሚያስፋፉ የዚህ ዓይነት ተግባር ለነርሱ መተው የለበ ትም ።

## ስለገቢና ወጪ ሁናቴ

### ስለ በጀት ፤

የመሃይምናንን ትምህርት ፕሮግራም ለማካሔድ ቋሚ በጀት ማስፈለጉ ግልጽ ነው ። ድኅነትና አለመማር የተያያዙ ሆነዋል ። ስለዚህ መሃይምናን ለት ምህርቶቻቸው ለመክፈል አለመቻላቸውን ፤ ፕሮግራም ያላቸው ገልጠዋል ። ከዚህም የተነሣ የመሃይምናን ትምህርት ከዳር እስከ ዳር በነፃ ይሰጣል ።

ግን ሥራዬ ብለው ለመሃይምናን ትምህርት የወር ወይም የዓመት በጀት ወስነናል ያሉ መሥሪያ ቤቶች የሚቀጥሉት ናቸው ።

የትምህርት ሚኒስቴር ሞያ ነክ ፕሮግራም
የምሥራች ድምፅ
ሕዝባዊ ኑሮ እድገት
ፊደል ሠራዊት

በወርም ሆነ በዓመት የቀሩት መሥሪያ ቤቶች የሚያገኙት ገቢና የሚያደ ርጉት ወጪ ፤ እጅግ አነስተኛ ነው ። የብዙዎቹ የዓመት በጀት ከመቶ አያል ፍም ። ፫፻ ወይም ፩ሺህ የሚደርስ በጀት ያላቸው ጥቂት ናቸው ።

በጀት አለን ካሉት ፲፮ መሥሪያ ቤቶች የአራቱ በጀት ብቻ ፮፻፹፩ ሺህ ብር ያህል ሲሆን ፤ የቀሩት የአሥራ ሁለቱ ግን ፪ሺህ ፱፻ ብር ያህል ብቻ ነው።

### ገ ቢ ፤

በጀት ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ገንዘብ ከየት እንዴትስ ያገኛሉ ?

ከመንግሥት
ከሕዝብ የሚገኝ መዋጮ
ከውጪ ርዳታ
በዓላትና ትርኢት በማዘጋጀት ዕቃ በመሸጥ ፤

በዓላትን በማዘጋጀት የሚገኝ ገንዘብ ፈጽሞ ቍጥር የሚገባ አይደለም ። አንዳንድ ቦታ ተማሪውን አስከፍሎ ትምህርቱ ራሱን እንዲችል ለማድረግ ተሞክሮአል ። ግን መሃይምናን ዓቅም እያነሣቸው ማስከፈሉ ይቀራል ። የግል ትምህርት ቤቶች ግን ከ፪ኛ ክፍል ጀምሮ እንዲከፍሉ ያደርጋሉ ። እዚያም የሚ ደርሱት ጥቂት ናቸው ። ይህ ሁሉ አነስተኛ ስለሆነ በዚህ ዓይነት የተመሠረ ቱት ፕሮግራሞች ዘላቂነት የላቸውም ። ሥራቸው ብልጭ ድርግም እያለ ፍሬ ቢስ ሆኖአል ።

ቋሚ የሆኑና ዘላቂ ሥራ ያላቸው ቋሚ በጀት ያላቸው ብቻ ናቸው ። ምንም እንኳን እነዚህ ድርጅቶች ያላቸው በጀት ፤ ፕሮግራማቸውንና ሥራቸውን አይሸፍንም ቢሉም ቅሉ ፤ ከሌላው ሲመዛዘን የተሻለ ውጤት ያሳያል ።

ስለዚህ ቋሚ ሥራ ከተፈለገ ፤ ቋሚ በጀት ያስፈልጋል ። ቋሚ በጀትም የሚገኘው ከመዋጮና ከበዓላት ዝግጅት ሳይሆን ከመንግሥት ብቻ ነው።ከመዋጮ የሚገኘው አነስተኛ ከመሆኑ በላይ ዘላቂነት የለውም ። ስለዚህ ቋሚ በጀት ከመንግሥት ተይዞ ተጨማሪ ከመዋጮና ከበዓላት ገቢ ማመንጨት ያስፈልጋል ።

ወጪ ፤

ብዙዎቹ በጀት ያላቸው ለምን ለምን ወጪ ያደርጋሉ ? በጀት ካላቸው ወጪው አብዛኛውን —

ለአስተማሪ ደመወዝ
ለትምህርት መሣሪያ
ለሌላ ሌላ ፤ ለምሳሌ ለመብራት

ገንዘብ ከተገኘ አስተማሪ ቀጥሮ ማስተማሩን ይመርጡታል ። እንደሚመስለው በጀት በመታጣቱ የተነሣ ፤ ነፃ አስተማሪ ይፈልጋሉ እንጂ ፤ ቀጥሮ ማስተማር ብዙዎቹ ይመርጣሉ ። ይህም የሆነው ፈቃደኞች አስተማሪዎች ላይ መተማመን ስለማይቻል ነው ። ስለዚህ ለቋሚ ቅጥር አስተማሪዎች በጀት አድርጎ ፤ ባይሆን ተጨማሪ ፈቃደኞችን ማከሉ ይሻላል ። ትምህርት ሚኒስቴር ፤ በየትምህርት ቤቱ ለሚያስተምሩ ወጣቶች ፤ ብር በወር አልፎ አልፎ ይሰጣል ። ይህ ቢስፋፋ ብዙ ይረዳል ።

በጀት የሌላቸው ድርጅቶች ብዙ ናቸው ። በጀት ከሌላቸው እንዴት ትምህርቱን ያካሔዱታል ?

የመሃይምናንን ትምህርት ከመደበኛ ሥራቸው ጋር
አደባልቀው ይሠራሉ አስተማሪ በነፃ ያገኛሉ ፤
የትምህርት መሣሪያና ቤት በነፃ ያገኛሉ ።

የመሃይምናን ትምህርት ያላቸው አንዳንድ መሥሪያ ቤቶችና ትምህርት ቤቶች ፤ ፕሮግራሙን ከሌላ ሥራቸው ጋር ደርበው ስለሚሠሩት ለዚሁ ሲባል ልዩ በጀት አያወጡም ። ለምሳሌ የግልም ሆነ የመንግሥት ት/ቤቶች ማታ ማታ ሌላ የትምህርት ፕሮግራም በንግድ መልክ ስላላቸው ፤ ለመሃይምናን ትምህርት በተለይ ወጪ አያደርጉም ። ከአስተማሪዎቹ አንዱን እንዲያስተምር ያደርጉታል ።

ከነዚህ አንዳንዶቹ የመሃይምናንን ትምህርት ደርበው የሚሠሩት የግል ጥቅምንም ፍለጋ ነው ። በገንዘብ ማታ ሆነ ቀን የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች ስማቸው ባካባቢው እንዲታወቅ ሲሉ ፕሮግራሙን ይጀምራሉ ።

ወይም ደግሞ መሃይምናንን አንድ ክፍል በነፃ ካስተማሩ በኋላ ፤ ሁለተኛ ክፍል እንዲገቡና ከፍለው እንዲማሩ ያደርጋሉ ።

ይህንንም የሚያደርጉት ትርፍ ቦታ ሲኖራቸው ነው ። ከፍለው ለሚማሩ ተማሪዎች ሁልጊዜ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ። ይህ ማለት ተማሪ ቤቱ ከፍለው በሚማሩት ከተያዘ መሃይምናንን አይቀበሉም ። ከዚህም የተነሣ በዛሬ ጊዜ የማታ ትምህርት በየከተማው እየሰፋ ሲሔድ ከየትምህርት ቤቱ የመሃይምናን ፕሮግራም እየቀነሰና እየተቋረጠ ሔዷል ። ቦታውን ለንግድ ለቅቋል ።

## በየድርጅቱ ስለሚማሩ መሃይምናን ተማሪዎች

ፆ ታ

መሃይምናንን የሚያስተምሩ ድርጅቶች አብዛኛውን ጊዜ የፆታና የዕድሜ ገደብ አያደርጉም ። ሴትንም ወንድንም እኩል ለማስተማር ተሰልፈዋል ። አን ዳንድ ድርጅቶች ለሴቶች ብቻ ባልትና ሞያ ለማስተማር የተመሠረቱ ስለሆነ ሴት ሲያስተምሩ ወንዶችንም ይጨምራሉ ። በጠቅላላው ግን በብዛት ከፍ ያለ ብልጫ ያላቸው ተማሪዎች ወንዶች ናቸው ።

ለዚህ አንዳንዶች ምክንያት ሲሰጡ የባህል ገደብ በሴቶች ላይ ስላለባ ቸው ፤ እምብዛም ለትምህርት አይመጡም ይላሉ ። ለምሳሌ ሴት ለምን ብላ ትማራለች የሚል አስተሳሰብ ዕንቅፋት ሆኖአል ።

ሌሎች ደግሞ ሴቶች የቤት ሥራ ስለሚበዛባቸውና ጊዜ ስለሚያንሳቸው ለትምህርት ሊመጡ አይችሉም ፤ ወይም ትምህርቱን ያቋርጣሉ ይላሉ ። በተለ ይም የምሽት ትምህርት ለሴቶች የማያመች ስለሆነ ፤ ቍጥራቸው ይቀንሳል ብለ ዋል ። ስለዚህ በየቦታው ለሴቶች ተስማሚ የሆነ የትምህርት ጊዜ መፈለግ ይኖርበታል ።

ዕ ድ ሜ ፤

በዕድሜ በኩል ደግሞ ብዙ ድርጅቶች ገደብ አያደርጉም ማለት ለመ ጠነ ትምህርት የደረሰውን ማንኛውንም ልጅ ወይም ጐልማሳ መሃይምን ይቀ በላሉ ። የማታ ትምህርት ቤቶች የመንግሥትም ሆነ የንግድ ፤

የመጣላቸውን ልጅና ጐልማሳ መቀበልና እኩል ማሰለፍን ያዘወትራሉ። በየከተማው የቀን ትምህርት ዕድል ያላጋጠማቸው ልጆች በየማታ የትምህርት ቤቱ ብዙ ቦታ ይዘዋል ። በቍጥር ማረጋገጥ ያቅታል እንጂ ፤ እንደሚታየው ከሆነ በየድርጅቱ የሚማሩት መሃይምናን በልጅነት ዕድሜ ያሉ ይመስላል ።

ከአሥራ ስድስት ዓመት በላይ የሆኑትን ብቻ እንቀበላለን የሚሉ መሥ ሪያ ቤቶች መጠነኛ ናቸው ። ከ፲፮ እስከ ፳፫ ዕድሜ አካባቢ ያሉት ሳይበዙ

አይቀሩም ። መወሰን ከሚኖርበት ነገሮች አንዱ የመሃይምናን ትምህርት ከየትኛው ዕድሜ እስከ የትኛው መሆን እንዳለበት ነው ።

የዕድሜ ገደብ ባይደረግም ቅሉ ፤ ጐልማሳንና ልጅን በአንድ ክፍል ማስተማሩ ችግር እንዳለው መገንዘብ ያስፈልጋል ። በዕድሜ የገፉት ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት ዝቅ ያለ ስለሆነ ፤ ምናልባት ወጣቱን መሃይምን ለማስተማር ጥረት ቢደረግ ይሻላል ።

## የትምህርት ፍላጎት ፤

የመሃይምናን የትምህርት ፍላጎት ምን ያህል ነው ወይም የመሃይምናን ትምህርት ተፈላጊነት አለውን የሕዝቡ ተቀባይነት እንዴት ነው ? ብዙ ድርጅቶች በየቦታው ብዙ ጥረት ያደርጋሉ ። የጥረታቸው መነሻ መሃይምናን ትምህርት ይፈልጋሉ ። እንዲያውም ተጠምተዋል በሚል እምነት ነው ።

የመሃይምናንን የትምህርት ፍላጎት ከቦታ ቦታ ይለያያል ። ከተማ ውስጥ ያልተማሩ ሰዎች በዚያም በዚህም ተምሮ ፤ ማንበብና መጻፍን ትንሽ ሒሳብ ለማወቅ ይጣጣራሉ ። በተለይም በየድርጅቱ የሚሠሩ ሠራተኞች መጻፍና ማንበብ ለሥራቸው ማስፈለጉን ከተረዱና ለእድገትም የሚረዳ መሆኑን ሲገነዘቡ ለመማር ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ።

የትምህርት ፍላጎታቸው ከፍ ብሎ የሚታየውና ከትምህርትም ገበታ የማይለዩት እነዚህ ናቸው ። ለሥራቸውና ለሕይወታቸው ወዲያውኑ ቀጥታ ጥቅም የሚያመጣ መስሎ ካልታያቸው ፤ መሃይምናን ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት እጅግ የቀዘቀዘ ነው ። ይህ ፍላጎት በተለይ በገጠር ቀዝቅዞ ይታያል ።

፩/ ማታ ሆነ ቀን የመሃይምናን ትምህርት ተከፍቶ በማስታወቂያም ተነግሮ ፤ የሚማር ይጠፋና የሚዘጋበት ጊዜ አለ ። እንዲህ ያለው ሁናቴ የዩኒቨርሲቲ ብሔራዊ አገልግሎት አስተማሪዎች በብዙ ቦታ እንደደረሰባቸው ፲፱፻ ፸፫ ዓ. ም. መጨረሻ ላይ ያቀረቡት ዝርዝር መግለጫ ያስረዳል ።

፪/ በመጀመሪያ ጊዜ በርከት ያሉ መሃይምናን ቢመዘገቡም ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ቍጥራቸው ይለዋወጣል ። በክረምት የሚበዙበትና በበጋ የሚያንሱበት ፤ ወይም በበጋ በዝተው በክረምት የሚያንሱበት ቦታ አለ ። ሠራተኞች «በሽፍት» በሚሠሩበት ቦታ እንዲሁ ቍጥራቸው ይለዋወጣል ።

፫/ ሁሉ ነገር በበጎ ፈቃድ ላይ ስለተመሠረተ የመሃይምናን ፍላጎታቸው በአንዳች ምክንያት ከፍተኛ ካልሆነ ፤ በሆነው ባልሆነው ምክንያት በትልቁም በትንሹም ከትምህርት ይቀራሉ ። ብቅ ጥልቅ ይላሉ ። ወይም እያረፈዱ ይመጣሉ ። አስተማሪውና ድርጅቶቹ ለዚህ እስካሁን ምንም መፍትሔ አላገኙም ። ብዙ ጊዜ በምክር ይታለፋል ። ቅጣት ሊሰነዘሩ የሚችሉ ትንሽ ናቸው ። ለምሳሌ በየወህኒ ቤት የሚማሩ ይገደዳሉ ። በወታደርነት የሚማሩ ቢቀሩ ርምጃ ይወሰድባቸዋል ። በሌሎች ቦታ እንዲህ ያለ ርምጃ መወሰድ አለመቻሉን ይገል

ጻሉ ። በየቦታው በልምምጥ ፤ በምክር ለማስተማር ይሞክራል ። ይህ ግን መሃይምናንን ትምህርታቸውን ከማቋረጥ አያግዳቸውም ።

ትልቁ ችግር እንግዲህ የመሃይምናን ትምህርታቸውን ማቋረጥ መሆኑ ነው ። ለፍላጎት ማነስ ምክንያት የሆነው ፤ ለሥራቸውና ለሕይወታቸው ትምህርቱ ትርጉም በማጣቱ ብቻ አይደለም ። በተለይ በገጠር ጠቀስ ቦታዎች የሚቀጥሉት ችግሮች በዚያም በዚህም የመሃይምናን ፍላጎት እንዲቀነስ ያደርጋሉ

የመጽሐፍና የዕቃ ችግር
መብራት ማጣት
በአስተማሪ በኩል የሚደርስ ጉድለት
የባለሥልጣኖች አለመተባበር
የመማሪያ ቦታ ችግር
የአንዳንድ ተማሪ ቤቶች ከመኖሪያ ሠፈር መራቅ
በባህል ምክንያት የሴቶች መከልከል
ገረድና አሽከር ጊዜ ማጣት

የነዚህም ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው ።

፩/ የመጻሕፍትና የመማሪያ ዕቃ ችግር ምን ያህል እንደሆነ ከላይ ተገልጿል ። የመሣሪያ እጥረት ለብዙ ነገር ዕንቅፋት መሆኑ ግልጽ ነው ።

፪/ መብራት በከተማ ብዙ ችግር አይመስልም ። የግልም ሆነ የመንግሥት/ ቤቶች የመብራት በጀት አላቸው ። በየገጠሩ ግን ማታ ማታ ሲያስተምሩ የመብራት ችግር ይገጥማቸዋል ። እንደልብ ለማንበብና ለመጻፍ የግድ በቂ የመብራት ኃይል ያስፈልጋል ። ለዚህ ዘዴ መፈጠር ይኖርበታል ። ለምሳሌ ጧት ጧት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ወይም ቀን ቀን ማስተማር ይቻላል ። ይህ መቼም ሙሉ ጊዜውን የሚያስተምር አስተማሪን ይጠይቃል ። አንዳንድ ቦታ ከአሥራ አንድ እስከ አሥራ ሁለት ተኩል የሚያስተምሩ አሉ ።

፫/ በአስተማሪ በኩል ብዙ ጉድለት መኖሩን የተጠየቁት ድርጅቶች ገልጸዋል።ይህም ከላይ እንደተመለከተው በበጎ ፈቃዳቸው ሲያስተምሩ ፤ በመቅረት ግል ሃይማኖታቸውን በማስተላለፍ ፤ በማርፈድ ፤ ባለመዘጋጀት ፤ ችሎታ በማነስ ፤ የመሃይምናንን ትምህርት ፍላጎት ይቀንሳሉ ። በቅጥር የሚሠሩት ግን ግዴታ በቊጥጥር ሥር ሆነው ይሠራሉ ።

፬/ የአካባቢውና የትምህርት ቤት ባለሥልጣኖች አለመተባበር ብዙ ችግር ሊያስከትል ይችላል ። የት/ቤቱ ዲሬክተሮች ወይም መምህራን ማታ ማታ የንግድ ትምህርት ይከፍቱና ፤ ለመሃይምናን ትምህርት ዕንቅፋት የሚሆኑበት ጊዜ አለ ። ከዚህም የተነሣ ፦—

፭/ የመማሪያ ቦታ ያጥራል ወይም ይጠፋል ።

፯/ በየገጠሩ ዋናው የመማሪያ ቦታ ት/ቤት ስለሆነ ፤ የትምህርት ቤቱ ከሠፈር መራቅ ችግርን አስከትሏል ። ት/ቤቱ ከከተማ ውጪ ከሆነ ሳይሠራበት ይቀራል ።

የገጠር ቤቶች የተራራቁ ናቸው ። እጅብ ያለ መንደር በየቦታው አለመኖሩ ለገጠር ሕዝብ ፕሮግራም ማዘጋጀት ታላቅ ዕንቅፋት ነው ። መሃይምናንንም በየዕለቱ መጥተው እንዳይማሩ ያደርጋቸዋል ።

## የመሃይምናን ትምህርት ፕሮግራም አስተማሪዎች

ብዙዎቹ የመሃይምናን ትምህርት ድርጅቶች አስተማሪ የሚያገኙት ከሁለተኛ ደረጃና ከኰሌጆች ነው ። በኢትዮጵያ ከ፯ኛ እስከ ፲፪ኛ ክፍል ከ፩፻ ሺህ በላይ ተማሪዎች አሉ ። ከእነዚህ አስተማሪዎች ማግኘት ቀላል ሆኖ ተገኝቷል ። የማግኛውም ዘዴ ፦

በየትምህርት ቤቱ ብሔራዊ ስሜት ነክ ገለጻ በማድረግ
በየትምህርት ቤቱ ክበቦች በማቋቋም
ለተማሪዎቹ በመጠኑ ገንዘብ በመክፈል
በየጊዜው የምስክር ወረቀት በመስጠት ።

ትምህርት ቤቶችና የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ጣቢያዎች ባካባቢያቸው ያለውን ሕዝብ ያስተምራሉ ። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም በየተደለደሉበት በመሃይምናን ትምህርት ለመሳተፍ ይሞክራሉ ። ግን ብሔራዊ የዩኒቨርሲቲ አገልግሎት መሥሪያ ቤት የመሃይምናንን ትምህርት ሥራዬ ብሎ ስለማይከታተለው ጥረታቸው ዘለቄታና ቋሚነት የለውም ። ተማሪው ሲለቅ ሥራው ይቆማል ።

በጠቅላላው አስተማሪ ለማግኘት ልፋት እጅግም አላስፈለገም ። ስለዚህም ያለ ደመወዝ በፈቃደኝነት የሚሠሩት በደመወዝ ከሚሠሩት እጅግ ይበልጣሉ ። በደመወዝ የሚያሠሩት በተለይ ትልልቅ መሥሪያ ቤቶች ናቸው ።

ትምህርት ሚኒስቴር
የምሥራች ድምፅ
ሕዝባዊ ኑሮ እድገት
ግል ትምህርት ቤቶች
ብሔራዊ ሎተሪ ፤

እንግዲያ አስተማሪ ማግኘቱ ችግር አይደለም።ችግሩ የት ላይ ነው ቢባል ትልቁ ችግር በአስተማሪ በኩል ፦

ሰዓት አለመጠበቅ
እክል ባጋጠማቸው ቊጥር መቅረት
ፕሮግራሙን ማቋረጥ
የማስተማር ችሎታ ማነስ

ይህ ዓይነት ችግር የመሃይምናንን ትምህርት ፍላጎት ያደከመዋልና በጣም የሚታሰብበት ነው ። እዚህ ላይ የተጠቀሱት ችግሮች በተለይ የሚገጥሙት በፈቃደኝነት በሚሠሩት አስተማሪዎች ላይ ነው ። በፈቃዱ ስለሠራ ምናልባት ይህን ያህል የሚያስገድደው ነገር አለመኖሩን በመመልከት በትልቁም ሆነ በትንሹ እክል ሲያጋጥመው ያረፍዳል ፤ ወይም ይቀራል ። ጨርሶም ያቆማል ። ከዚህም የተነሣ ይህ ሲደጋገም የመሃይምናን ፍላጎት ይቀዘቅዝና ትምህርቱን ወደመተው ይመራቸዋል ። መሃይምናንም በፈቃዳቸው ስለሚማሩ እምብዛም ግዴታ አይሰማቸውም ። ስለዚህ አስተማሪውም ተማሪውም በፈቃደኝነት ስለ ተሰበሰቡ ማንኛውም ዓይነት ዕንቅፋት ፕሮግራሙን ያፈርሰዋል ። ከዚህም የተነሣ ብዙ ሪፖርት እንደሚያሳየው የልፋት ሁሉ ውጤቱ «ተጀምሮ ነበር ግን ተቋርጧል» የሚል ይሆናል ።

በፈቃደኝነት ከሚያስተምሩት ወጣቶች ውስጥ ፤ ለጊዜው የስሜት ግለት የገፋፋቸውና በሥራው ላይ ግን ያለው ጥረትና ድካም ይህን ግለታቸውን ሊያ ቀዘቅዘው ይችላል ። በተለይ የመብራት ፤ የመጻሕፍት ፤ የጽሕፈት መሣሪያ እጦት ወይም የቦታ ርቀት ፤ ዝናምና ብርድ ችሎ በፈቃደኝነት ለረጅም ጊዜ መሥራት ከፍተኛ ጥንካሬን ይጠይቃል ። እርግጥ ተቈጣጣሪ በየቦታው አለ ተብሎ ተገልጿል ። የት/ቤቱ ዲሬክተር ወይም የክበብ አባሎች ይቈጣጠራሉ ። በፈቃደኝነት ለሚማሩትና ለሚያስተምሩት ቍጥጥር ይህን ያህል አይረዳም ።

የችግሩ መኖር የሚያሳየው የመቈጣጠሪያው ዘዴ ትክክል አለመሆኑን ወይም ቍጥጥር የማያድነው መሆኑን ነው ። ስለዚህ መሠረቱ ካላማረ ቍጥጥር ሊያድነው አይችልም ማለት ነው ።

ጊዜ ካለመጠበቅና ከማቋረጥ ሌላ፤ በአስተማሪ በኩል የሚደርሰው ጉድ ለት የማስተማር ችሎታ ማነስ ነው ። እርግጥ ከተጠየቁት መሥሪያ ቤቶች የማስተማር ዘዴ እንሰጣለን ያሉ አሉ ። ከነዚህ ብዙዎቹ የማሠልጠኛ ድር ጅት ያላቸው ናቸው ። ዩኔስኮ ሙያ ነክ ፤ ምሥራች ድምፅ ፤ ፊደል ሠራዊት ሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ናቸው ። የቀሩት ቢበዛ መግለጫ ይሰጧቸው ይሆናል ። ስለዚህ ከየሁለተኛ ደረጃ ተውጣጥተው መሃይምናንን ለሚያስተምሩት በተለይ መሃይምናንን በደረጃቸውና ችሎታቸው መጠን፤የማስተማር ዘዴ አይሰ ጣቸውም ። የሚጠቀሙት ያው ራሳቸው በተማሩበት ዘዴ ነው ። ክፍል እንደ ገቡ በመሃይምናኑ ላይ ማስተማርን ይለማመዳሉ ማለት ነው ። አንዳንዱ እርግጥ ደኅና አቀራረብኖሮት መሃይምናንን ሊያረካና ለትምህርቱ ሊያተጋ ቸው ይችላል ። ሌላው ግን በአቀራረቡ እጥረት መሃይምናን ሊረዱት ወይም ሊከተሉት ያቅታቸውና ተስፋ ቈርጠው ትምህርቱን ያቋርጣሉ ። መሃይም ናን በበጎ ፈቃዳቸው ቢመጡም ችግር እንዳላቸው መረዳት ያስፈልጋል ። ቀን ሲሠሩ ውለው ማታ ሲማሩ መድከማቸው ስለማይቀር አቀራረቡ አሰልቺ ከሆነ ፍላጎታቸውን ይቀንሳል ። ከዚህም ሌላ የቋንቋ ችግር ያላቸው መሃይምናን አሉ ። ልጅ ፤ ጐልማሳ ፤ ወንድና ሴት አብረው አንድ ክፍል ውስጥ ይማራሉ ።



2*

በልዩ ልዩ ሥራ የተሠማሩም ፤ ለምሳሌ የፋብሪካ ሠራተኛ ፤ ገረድ ፤ ገበሬ ፤ ሊስትሮ አብረው በአንድ ክፍል ይማራሉ ። የነዚህ ሁሉ ትምህርት የመቀበል ችሎታ ስለሚለያይ እነዚህን በአንድነት ለመምራትና ለማስተማር ከአስተማሪው ብዙ ችሎታን ይጠይቃል ።

በተለይም ለአስተማሪው በየትምህርቱ ፍቱን የሆነ መምሪያ ስላልተዘጋጀ፤ የማስተማሩ ዘዴ ቅጥ ያጣል ።

ስለዚህ የመሃይምናንን ትምህርት ፍሬአማ ለማድረግ በጥናትና ምርምር የተመሠረተ የማስተማሪያ ዘዴ ለየትምህርቱ አዘጋጅቶ በዚሁ መሠረት አስተማሪዎች እንዲያስተምሩ መምራት ነው ።

## ስለመሃይምናን የትምህርት ጊዜ

የመማሪያው ጊዜ ከቦታ ቦታ ይለያያል ። በከተማ ላሉት መሃይምናን ፤ በግብርና ላሉት ገጠር መሃይምናን ፤ በከተማ ላሉት ሴቶች መሃይምናን ፤ በተለያየ ጊዜ ትምህርት ይሰጣል ።

ለከተማ መሃይምናን

በከተማ ላሉ መሃይምናን አብዛኛውን ጊዜ ትምህርት የሚሰጣቸው ማታ ማታ ነው።በጣም የተለመደው ጊዜ ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ተኩል እስከ ፪ ሰዓት ተኩል ነው የሚማሩትም ፫ የትምህርት ጊዜ ነው ። ይህ እንደ ልማድ ወደ መሆኑ ላይ ነው ። በየሳምንቱ ከሰኞ እስከ ዓርብ (፭X፫) ፲፭ የትምህርት ጊዜ አለ ። የመሃይምናን ትምህርት የሚሰጠው በየትምህርት ቤት መሆኑ ግልጽ ነው ። ስለዚህ ትምህርት ቤቱ ሲከፈት የመሃይምናንንም ትምህርት ይከፈታል ። ትምህርት ቤቱ ሲዘጋ የመሃይማናንም ትምህርት አብሮ ይዘጋል ።

ብቻ የግል ትምህርት ቤቶችና ማታ ማታ በክፍያ የሚያስተምሩ መንግሥት ትምህርት ቤቶች በክረምትም ጭምር ያስተምራሉ ። ይህም የሚሆነው በየትልልቅ ከተሞች ብቻ ነው ። በአነስተኞች ከተሞች ትምህርት ቤቱ ሲዘጋ ሁሉም ይዘጋል ። ስለዚህ በትልልቅ ከተሞች ብቻ በበጋና በክረምት የመሃይምናን ትምህርት ይካሔዳል ።

በክረምት ወራት ቀን ቀን የሚያስተምሩ ድርጅቶች አሉ ። ብሔራዊ ሎተሪና የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ጣቢያዎች አልፎ አልፎ ተማሪ በብዛት እየቀጠሩ ያስተምራሉ ። ይህን ትምህርት የሚከታተሉት ጐልማሶች መሃይምናን ሳይሆኑ ልጆች ናቸው ።

ለገበሬዎች ፤

በየገጠሩ ለገበሬዎች ትምህርት የሚሰጡ ድርጅቶች በተለይ የሞያ ነክ የጐልማሶች ትምህርት ፤ የምሥራች ድምፅ ፤ የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ጣቢያዎች ናቸው ።

እነዚህ ገበሬዎችን ቀን ቀን ብቻ ያስተምራሉ ። ትምህርቱ ለገበሬዎች በሚያመችበት ወቅት በበጋ ያስተምራሉ ። በክረምት የአዝመራ ጊዜ በመሆኑና ክረምቱም ስለሚያስቸግር ትምህርት ይቋረጣል ።

ለሴት መሃይምናን ፤

መሃይምናን ሴቶች ትምህርት ቤት ለመሔድ ብዙ ችግርና ተቃውሞ አለባቸው ። ከዚህም ጐልተው የሚታዩት ፤ የቤት ሥራ መብዛት ፤ ሴት ብትማር ምን ያደርጋል የሚለው ባህል ፤ በምሽት ሴቶች መከተት ስላለባቸው ነው ።

ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ድርጅቶች ለሴቶች ከሰዓት በኋላ ከ፱-፲፩ ያስተምራሉ ። የዚህም ትምህርት በቀለም ብቻ ሳይወሰን የሴት ባልትናንም የሚጨምር ነው ።

መመዝገቢያ ጊዜ ።

ለመሃይምናን ትምህርት መመዝገቢያ ጊዜ ብዙዎች ድርጅቶች የላቸውም ። መሃይምናኑን እንደመጡ ይቀበሏቸዋል ። አንዳንዶች ተማሪ የሚበዛባቸው ትም/ ቤቶች በመስከረምና ጥቅምት ካልተመዘገባችሁ አንቀበልም የሚሉ አሉ ። የዚህ ዓይነቱ በመጠኑ ናቸው ።

ተማሪው እየተንጠባጠበ ሲመጣ ለማስተማሩ ብዙ ችግር ይፈጥራል ። ክፍሉ ውስጥ ያሉት ችሎታቸው ስለሚዘበራረቅ ለአስተማሪው ችግር ይፈጥራል ። የብዙዎችን ፍላጎት ትምህርቱ ሳያረካ ይቀርና ትምህርት ይቋረጣል ።

ስለዚህ ለአንድ ኮርስ በተወሰነ ጊዜ መዝግቦ ፤ ለተወሰነው ግብ ከደረሱ በኋላ ፤ አዲስ ገቢዎችን መቀበልና ማስተማር ደንብ መሆን አለበት ።

የትምህርት ጊዜ ርዝመት ።

ብዙው ትምህርት ማታ ማታ ከ፲፪ ፡ ተኩል - ፪ ፡ ተኩል ለሦስት ሰዓት እንደሚሰጥ ተገንዝበናል ። እንደዚህ እያስተማሩ በስንት ጊዜ ውስጥ ትምህርቱን ያስጨርሳሉ ።

ለዚህ ጥያቄ የተሰጠን መልስ የሚቀጥለው ነው ። ብዙዎች ድርጅቶች በ፫-፬ ወር ውስጥ ፊደል ንባብና ጽሕፈት እናስታምራለን ሲሉ የቀሩት ግን እስከ ፯ ወር እናስተምራለን ይላሉ ። የአንደ ዓመት ትምህርት የሚሰጡ እጅግ ትንሽ ናቸው ። ስለዚህ ብዙዎቹ የ፫ ፤ የ፬ ፤ የ፳ ወር ትምህርት ይሰጣሉ ማለት ነው ።

ስለዚህ በየሳምንቱ ፲፳ ሰዓት እየተማሩ በ፫ ፤ ፬ ፤ ፯ ወሮች ስንት የትምህርት ጊዜ እንዳለ ቀጥሎ ተመልክቷል ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| በሦስት ወር | 3 x 4 x 15 | 180 | የትምህርት ጊዜ |
| በአራት ወር | 4 x 4 x 15 | 240 | የትምህርት ጊዜ |
| በስድስት ወር | 6 x 4 x 15 | 360 | የትምህርት ጊዜ |

ይህን የትምህርት ጊዜ ማወቅ ለምን ይጠቅመናል ለመሃይምናን ትምህርት እቅድ ለማውጣት ይረዳናል ።

ትምህርቱ ብዙ ጊዜ በጀት ፤ አስተማሪ ወይ ቦታ ጠፍቶ ስለሚቋረጥ ይህ እንዳይሆን በእቅድ ለመነሣት ይረዳናል ። ለምሳሌ ፩፻፹ የትምህርት ጊዜ አንድ አስተማሪ ቢቀጠርና በአንድ ትምህርት ጊዜ ዜሮ ሳንቲም ቢሰጠው ለ፩፻፹ ሰዓት ፺ ብር ያስፈልጋል ። በዚህ ሂሳብ ፺ ብር በአንድ ክፍል ለ፵ ተማሪ ያህል ለ፫ ወር ማስተማር ይቻላል ማለት ነው ። በዚህ መሠረት ለብዙ ተማሪ በጀት ለማዘጋጀት ይቻላል ።

፩/ ለአስተማሪዎች በየትምህርት ሰዓት አበል ይታሰብላቸው ።

፪/ አስተማሪዎች በየቀኑ የሚማሩትን የተማሪዎች ፊርማ አጠራቅመው ማቅረብ አለባቸው ።

፫/ የክፍሉ ተማሪዎች ማነስና መብዛት የአስተማሪውን አበል እንዲቀነስበት ወይም እንዲያበዛለት መደረግ አለበት ። (ለምሳሌ ፵ ጀምረው እንደሆነ ወደ ፳ ከወረዱ ከሌላ ክፍል ጋር መዳበልና አስተማሪውን ማሰናበት ወዘተ ፤ ከ፵ ጨምረው ፸ ከሆኑ ክፍሉ በሁለት ክፍል እንዲያስተምር ማድረግ ።

፬/ ለትምህርት ጊዜ ተቆጣጣሪ የየትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ፤ የዕድር ኃላፊ ወይም ሌላ የማዕከላዊ ድርጅት ወኪል መሆን አለበት ።

## በየድርጅቶቹ መሐል ያለ ግንኙነትና መተባበር

መሃይምናንን የሚያስተምሩ መሥሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ግንኙነት አላቸውን ይተባበራሉን የሚያስተባብራቸው መሥሪያ ቤት አለን ብለን ጠይቀን ነበር ።

፩/ ግንኙነት እናደርጋለን የሚሉ መሥሪያ ቤቶች ፤ ከፍ ያሉትን ድርጅቶች በየፊናቸው ርዳታ ይጠይቃሉ ። የሚጠይቁትም የርዳታ ዓይነት ተመሳሳይ ነው ።

መጻሕፍትና መሣሪያ ፤ አስተማሪ ፤ ገንዘብ ፤ ምክር

ይህን ከፍተኛ መሥሪያ ቤቶችን ርዳታ መጠየቅን ትብብርና ግንኙነት ይሉታል ። ብዙ ጊዜ የሚጠየቁትም መሥሪያ ቤቶች የሚከተሉት ናቸው ።

ትምህርት ሚኒስቴር ።
ፊደል ሠራዊት
ቀ. ኃ. ሥ. ዩ.
ሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት
የምሥራች ድምፅ ።

እነዚህ ተጠያቂ ድርጅቶችም እምብዛም እርስ በርሳቸው ግንኙነትና መተባበር የላቸውም ። እያንዳንዱ በበኩሉ መሃይምናንን ለማስተማር ይጥራል ። አንድ ድርጅት ተገናኝተው የሚገጥማቸውን ዕንቅፋት ለመወያየትና ልምም

ድን ለመከፋፈል የሚያደርጉት ጥረት አጥጋቢ ሆኖ አላገኙትም ። አነስተኛ ድርጅቶችም ርዳታ ሲጠይቋቸው ያላቸውን ይለግሳሉ ።

ሆኖም ርዳታ ጠያቂ ድርጅቶች ርዳታ ጠይቀው መልስ አለማግኘታቸውን ደግጋመው ይናገራሉ ። ቢሆንም ግንኙነት ማድረጉ ጠቃሚ መሆኑን ይገልጻሉ።

፪/ ግን አብዛኞቹ የመሃይምናን ፕሮግራም የሚመሩ መሥሪያ ቤቶች ማን ንም ርዳታ ጠይቀን አናውቅም ወይም ምንም ዓይነት ግንኙነት ከሌላ ተመሳ ሳይ ድርጅት ጋር አላደረግንም ይላሉ ። ከዚህም የተነሣ መሃይምናንን በማስ ተማር ውድድርና ግጭት አላጋጠማቸውም ። በራሳቸው ብቻ መጣራቸውን ይገ ልጻሉ ።

ሆኖም የተጠየቁት መሥሪያ ቤቶች በሙሉ ፤ ትብብርና ግንኙነት አስፈ ላጊ መሆኑን ፤ ደጋግመው ጠቅሰዋል ። ስለዚህ ጉዳይ አስተባባሪ ድርጅት የለም ብለዋል ። ከዚህም የተነሣ አንድ አስተባባሪ ድርጅት መፈጠር አለበት ይላሉ ። ትብብሩስ ለምን ያስፈልጋል ለሚለው ፦—

መጻሕፍት በጋራ ለማዘጋጀት
ፕሮግራም በጋራ ለማዘጋጀት
ገንዘብ በጋራ ለመሰብሰብ
የውይይት ግንኙነት ለማድረግ
ፈቃደኛ አስተማሪ ለማግኘትና ለማሠልጠን
ስለመሃይምናን በጋራ ምርምር ለማድረግ ፤

አ ጠ ቃ ላ ይ ።

# በመሃይምናን ትምህርት የሚደርሱ ችግሮችና ፤ መፍትሔ ይሆናሉ የተባሉ ሃሳቦች

የመሃይምናንን ፕሮግራም የሚመሩ መሥሪያ ቤቶች የሚመስላቸውን ችግሮችና መፍትሔውን እንደሚከተለው አቅርበዋል ።

ሀ- በቅደም ተከተል ችግር ብለው የሚያቀርቡት እንደሚከተለው ነው ።

| | |
|---|---|
| የመጻሕፍት እጥረት | ርዳታ ጠይቆ አለማግኘት |
| የገንዘብ እጥረት | የፈቃደኛ አስተማሪዎች ኃላፊነት ማነስ |
| የቦታ እጥረት | የባለሥልጣኖች ፕሮግራሙን አለመደገፍ |
| የሚማር መሃይምን እጥረት | የትምህርት ቤት ከከተማ መራቅ |
| የትምህርት መሣሪያ እጥረት | የመብራት እጦት |
| የአስተማሪ እጥረት | የተማሩትን መልሰው መርሳት |
| የፕሮግራሙ ከኑሮ ጋር አለ መስማማት | አሠሪዎች በፈለጉበት ጊዜ ሠራተኞችን ስለሚያሠሩ መሃይምናን የሆኑ ሠራ ተኞች ትምህርታቸውን ማቋረጥ ፤ |

ለ- የሚቀጥሉት መፍትሔ ይሆናሉ ተብለው የቀረቡ አስተያየቶች ናቸው።

፩- የመሃይምናንን ሕይወት ፤ ችግር ፤ ፍላጎት የሚያረኩ ምንባብ ለየቦታው ሁናቴ ማዘጋጀት ፤

፪- በጎ ፈቃድ ብቻ ስለማይበቃ ለድርጅቶች ጥብቅ ትእዛዝ ተላልፎ ያስተምሩ ፤

፫- የመሃይምናን አስተማሪ ገንዘብ ተከፍሎት ወይም ግዴታ ገብቶ ያስተምር ፤

፬- ከማዕከላዊ መሥሪያ ቤት ቊጥጥር ይኑር ፤

፭- ቤተ መጻሕፍት በየገጠሩ ይቋቋሙ ፤

፮- የየክፍሉ የሥራ ፍሬ በየጊዜው ይታተም ፤

፯- የመሃይምናን ትምህርት መስጫ ጣቢያ ት/ቤት በሌለበት አካባቢ ይቋቋም ፤

፰- ለመሃይምናን አስተማሪዎች የሚሰጠው ሠርተፊኬት ዋጋ ይኑረው ፤

፱- መሃይምናን እንዲማሩ መንግሥት በሕግ ያስገድድ ፤

፲- ለትብብር ግንኙነት አንድ አስተባባሪ ድርጅት ይኑር ። ይኸውም ፦

መጻሕፍትን በጋራ ለማዘጋጀት
ፕሮግራም በጋራ ለማዘጋጀት
ገንዘብ በጋራ ለመሰብሰብ
ፈቃደኛ አስተማሪ ለማግኘትና ለማሠልጠን
ስለመሃይምናን በጋራ ምርምር ለማድረግ ፤

፲፩- ቋሚ በጀት ያስፈልጋል ። ከመዋጮ የሚገኝ አነስተኛ ከመሆኑ በላይ ፤ ዘላቂነት የለውም ። ስለዚህ ቋሚ በጀት ከመንግሥት ተይዞ ፤ ተጨማሪ መዋጮና ከበዓላት ገቢ ማመንጨት ያስፈልጋል ።

፲፪- ትምህርት ቤቶች ማታ ማታ ለንግድ ስለተያዙና ለመሃይምናን ትምህርት ቦታ ስለጠበበ በጥብቅ የሚታሰብበት ችግር ነው ።

፲፫- ለመሃይምናን ትምህርት አስተማሪዎች የማስተማር ዘዴ ትምህርት ይሰ

፲፬ ጣቸው ፤

- ለመሃይምናን ሥርዓተ ትምህርትና የአስተማሪ መምሪያ ለየትምህርቱ

፲፭ በጥናትና ምርምር ተዘጋጅቶ ይቅረብ ፤

- ለሴቶች ተስማሚ የሆነ የትምህርት ጊዜ መፈለግ ይኖርበታል ፤

- የመሃይምናን ትምህርት ፕሮግራም የሚጀመርበትና የሚያልቅበት ጊዜ የታወቀና የተወሰነ መሆን አለበት ።

- በየቤተ ክርስቲያኑና በየመስጊዶቹ ለመማሪያ የሚሆኑ ቤቶች ወይም ክፍ ሎች አይጠፉም ። ከቤተ ክርስቲያንና መስጊድ ኃላፊዎች ጋር ተገናኝቶ በውል ተጨማሪ ቦታ ለማግኘት መሞከር ይጠቅም ይሆናል ። የአካባቢ

፲፯ ውንም መሃይምናን ለማስተማር ይመቻል ።

፲፰- በየቤተ ክርስቲያኑና ቤተ መስጊድ ዕቃ ቤቶች አሉ። ከነዚህ የዕቃ ቤቶች ዋና ተግባር አንዱ ፤ መጻሕፍትን ማስቀመጥ ፤ መጠበቅና በተፈለጉ ጊዜ መስጠት ፤ ማዋስ ነው ። ዕቃ ቤት ጠባቂዎች የአካባቢውን ሕዝብ ደኅና አድርገው ያውቃሉ ። ብዙ መጻሕፍት ከታተሙ ፤ ለመሃይምናን እንዲደ ርስ ሲባል ፤ እነዚህን ዕቃ ቤቶች ከትንሽ ማሻሻል ጋር ለመጠቀም ይቻ ላል ። አዲስ ቤተ መጻሕፍት ከማቋቋም ይልቅ እነዚህኑ አሻሽሎ ፤ በነዚሁ አማካይነት ለመሃይምናን በየዕለቱ የሚነበቡ ጽሑፎች ማቅረብ ይቻላል

፲፱- ተጨማሪ ቋሚ አስተማሪ ለማግኘት በልማድ የሚያስተምሩትን የንባብ ቤትና የቁራን ቤት አስተማሪዎች አሠልጥኖ ማሠማራት ነው ።

እነዚህን ባህላዊ አስተማሪዎች በየቦታው ሰብስቦ ዘመናዊ የማስተ ማር ዘዴ ኮርስ መስጠት ፤ ከዚያም ማስተማሪያ መጻሕፍትንና ጥቁር ሠሌ ዳን ሰጥቶ መልቀቅ ብቻ ይበቃል ። እነርሱ ራሳቸው በየግቢው ጥላ ሥር ካገር አገር ሔዶ ማስተማር ልምምድ ስላላቸው አያስቸግሩም ። ከሕዝቡ አነስተኛ አበል እየተቀበሉ ሊያስተምሩ ይችላሉ ። የሕዝቡን ባህልና ስሜት ስለሚያውቁ መሃይምናንን ለትምህርት በተሻለ ዘዴ ሊስቡ ይች ላሉ ። የዛሬ ወጣት አስተማሪ ግን ኑሮው ከሕዝቡ ራቅ ያለ ስለሆነ ፤ ከፍ ያለ ገንዘብ ይጠይቃል ። በአስተሳሰብም ከሕዝቡ ራቅ ያለ ነውና ብዙ አይስባቸውም ።

ባህላዊ አስተማሪዎችን በዘመናዊ ዘዴ ማሠልጠን ግዴታ ነው ። ኢት ዮጵያውያን ዩኒቨርሲቲ መምህራን ባለፈው ክረምት በርከት ላሉ ባህላዊ አስተማሪዎች ዘመናዊ ማስተማር ዘዴ ሰጥቶ ፤ በቅርቡ ፴፫ ጥቁር ሠሌዳ

ሰጥቷቸው በማስተማር ላይ ናቸው ። የሚሰጡት ውጤት ብዙ ተስፋ ያለው ስለሆነ ፤ ይህን ዘዴ መጠቀም ያሻል ።

፰- የመሃይምናን ትምህርት ከኑሮ ጋር አለመስማማቱ መሃይምናን እንዳይማሩ አድርጓል ። የተማሩትንም ይረሳሉ ይባላል ። ይህን ለመቋቋም ብሔራዊ ሥነ ጽሑፍ ድርጅት ለመሃይምናን ሲባል መቋቋም ይኖርበታል ።

እንደዚህ ያለ በብሔራዊ ደረጃ የተቋቋመ ድርጅት ለመሃይምናን በሚያስፈልጉት ጽሑፎች ላይ ምርምር እያደረገ ፤ በብዛት በርካሽ እያተመ ፤ ማደል ይኖርበታል ። ለምሳሌ ፤ በአጭር ዘዴ ፊደል መማሪያን ይመረምራል ። ድርቀት በሚበዛበት አካባቢ ውኃ እንዴት እንደሚገኝ ፤ ቤት በቀላሉ እንዴት እንደሚሠራ ፤ ወይም ወባና ዓይን በሽታ በሚበዛበት ቦታ ስለነዚህ ማደል ። ስለአስተራረስም ሆነ ስለሌላ ኑሮ ጠቀስ በርከት ያሉ ቀላል ድርሰቶች ማዘጋጀቱ ፤ ከፍተኛ ጥቅም አለው ። በሕዝቡ የማንበብ ልማድን ይፈጥራል ። ምንም እንኳን ሽማግሎች «እንግዲህ ወዲያ ምን ያደርግልኝ - - - እማራለሁ» ብለው ባይማሩ ፤ ብዙው ሕዝብ ጐልማሳ ወጣት ነውና ጐልማሳውን ለንባብ ይማርካል ፤ የሚያነበው ያገኛልና ።

በነዚህ ድርሰቶች አማካይነት የንባብና ጽሕፈት ትምህርት ዋጋ ያገኛል ። የችግር ማስወገጃ የሚሆን ዕውቀት ፤ ዘዴ ፤ ብልሃት ፤ ጥበብ ፤ ከድርሰቶቹ ስለሚቀስሙ ፤ የማያነበው ለማንበብ ምክንያት ያገኛል ፤ ይጥራልም ።

፱- አንድ ታላቅ የሆነ የመሃይምናን ትምህርት ፕሮግራም ከሚፈጥርና ጣቢያዎች እያቋቋመ ሆነ ወይም ትምህርት ቤት እየከፈተ ከሚሠራ ፤ አሁን ባሉት ድርጅቶች አማካይነት ቢሠራ ፤ ፍሬው ከፍ ያለ ይሆናል ። አዲስ ጣቢያዎች መክፈት ከትምህርት ቤቶች ፤ ከሕዝባዊ ኑሮ እድገት ጣቢያዎች ፤ ከእርሻና ከጤና ገጠር ሠራተኞች ጋር ፍሬ ቢስ ውድድር ማድረግ ነው ። ከላይ የተባሉት በየገጠሩ ተሠማርተዋል ። ግን ተባብረው የሚሠሩ አይመስልም ። ሌላ የ«መሃይምናን ትምህርት ጣቢያ» የተባለ ከሚከፈት ይልቅ ፤ ከላይ የተጠቀሱትን ዘረክረክ ያሉትን ድርጅቶች እንዴት ለመሠረተ ትምህርት ዓላማ ሊውሉ እንዲችሉ መርዳት ፤ መምራት ይበልጣል። በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያኖችንና ቤተ መስጊዶችን በየቦታው ሊገለገሉባቸው ይችላሉ ።

ስለዚህ የመሃይምናን ትምህርት ድርጅት በብሔራዊ ደረጃ የሚከተሉትን ክፍሎች አስፋፍቶ ቢመራና የማስተማሩን ተግባር በየድርጅቱ ቢያሠራ ተስፋው ብዙ ይመስላል ።

የመሃይምናን ትምህርት ምርምርና ምንባብ ዝግጅት ክፍል
የበጀት ክፍል
የመሃይምናንን ትምህርት ፕሮግራም አስተባባሪ ክፍል ፤

## ስለመሃይምናን ትምህርት ከተጻፉ ጽሑፎች በጥቂቱ

ብሔራዊ ፊደል ሠራዊት ፤

ብሔራዊ ፊደል ሠራዊት ማኅበር ከ፲፱፻፶፯ — ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. የፈጸማቸው የሥራ መግለጫ ፤ ሁሉ ይማር የፊደል ሠራዊት ማኅበር መግለጫ ።

የምሥራች ድምፅ ፤

Yemisrach Dimts Annual Report July 1970 – June 1971.

የምሥራች ድምፅ መሠረተ ትምህርት ክፍል ዓመታዊ የስታቲስቲክ ሪፖርት ነሐሴ ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ።

የሸዋ ጠቅላይ ግዛት ት/ቤቶች ጽ/ቤት ፤

የጐልማሶችና መሃይምናን ትምህርት ሥራ ውጤት
ስታቲስቲካዊ መግለጫ ፤ ፲፱፻፷፫ ዓ. ም.

የኮልፌ ቁጠባ ቤትና የከተማ ሕዝብ ኑሮ እድገት ጣቢያ አገልግሎት ። ፲፱፻፷፫ ዓ. ም.

ሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ፤

የወረዳ እድገት ጣቢያዎች ዝርዝር ፲፱፻፷፫ ዓ. ም.

ማሞ ከበደ

የአማርኛ ፊደል ማስተማሪያ ዘዴዎች ፲፱፻፷፫ ዓ. ም.